# ሁለት ዓይነት ሠርጎች



ኣዲስ ሚስት ለማግባት ሰርግ ተሰርጎ
ታላቁ ወንድሜ ዳስ፣ ድግስ ኣድርጎ
ጮማውና ቁርጡ፣ ክትፎውን ድግሶ
ጠላውና ጠጁን እንደ ውሀ ኣፍሰሶ
ቀይ-ወጥ፣ ኣልጫው፣ ዱለቱና ዝግኑ
እንጀራው፣ ኣምባሻው፣ ኣረ ምኑ፣ ምኑ!
ዘፋኙም ዘፈነ፣ ኣዝማሪው ዘመረ
እስክስታው፣ ጭፈራው ሲደለቅ ታደረ



ወንድሜም ከሃብቱ ብዙ ሺሕ ብር ከስሮ!
የወጣውስ ገንዘብ ስንቱ፣ ማንስ ቆጥሮ...
ዓላማውስ ነበረ ስሙ እየተጠራ
የሠርጉን ሁኔታ ተነስቶ ሲወራ
"ደገሶ፣ ኣበላ!" ብለው ሊያወድሱት፣
ስሙን እየጠሩ ብዙ እንድያሞግሱት።
ሆዳቸውን ሞልተው እስኪይዛቸው ቁንጣን
ቡናስ መቸ ቀረ፣ ተከትሎም ዕጣን
የኣፋቸው ፋተታ፣ የበሉት በርበሬ
በሣልስቱ ነበር የሰማነው ወሬ፤



"ጠላቸው ቅራሪ፣ ጠጃቸው ኮምጣጤ
ፊልተሩም መቅጠኑ፣ ከንቱ ውሀ ብጤ
ቢራው ጋዙ ነፍሷል፣ ዊስኪው ተበርዟል
ቁርጡስ መች ሰባ፣ ወጡ ጨው በዝቶታል
ክትፎው ምኑ ቅጡ፣ ሚጥሚጣም የለውም፣
ዱለቱ ኣልተቁላላም፣ ሓሞት ኣልገባውም..."

እንዲህ ሲያጣጥሉ፣ ኣቃቂር ሲያወጡ
በልተው ለሓሜት ነው፣ ኣረ ምኑ ቅጡ!
የሰው ፊትን ሲያዩ ከንቱ ሲያሞግሱ
ኋላም ዘወር ብለው ወሬ ሲያናፍሱ
ለተጋቡት እንጂ፣ ምናቸው ለነርሱ
ባይጠሩም ይቅር፣ እስከነ ድግሱ
ካለፈስ በኋላ ለከንቱ ይወራል፣
ወንድሜም ሲጸጸት፣ ሲያዝን ይኖራል...

ታናሽ ወንድሜ ግን ከታላቅ ተምሮ
ድግስ አልደገሰ፣ አልሰማ እሮሮ
“ስምህ እንዲከበር፣ እንዲሞገስልኝ
“አምላኬ ምከረኝ፣ ዘዴ ፍጠርልኝ፤
“አዕምሮየን ክፈት፣ አረ ምን ይሻላል?”
እያለ ሲፀልይ፣ ሲሰግድ ይውላል
አውጥቶ አውርዶም ብዙ ያሰላስላል…
ከዚያም በሠርጉ ቀን አንድ መላ መትቶ
የቅርብን ሰው ብቻ እራት ብጤ አብልቶ
ትዳሩን ጀመረ በጥሞና ገብቶ፤
ከዚያም ለሠርግ ብሎ ያኖረውን ገንዘብ
ምን እንደሚሠራ ይጀምራል ማሰብ…



ከተወለድንበት ከቀያችን መሃል
የሁሉን ሰው ችግር ጠይቆ ያጠናል
መሃንዲስም ይዞ ፕላኑን ያወጣል
መሬት የሚነድል ቆፋሪ ያስመጣል
በትንሽም ሞተር ስቦ እያስወጣ
ሰፈሩን በሙሉ ንጹሕ ውሃ አጠጣ
ከሰው የተረፈውን ከብት፣ እንስሳ ሁሉ
ወፍና ዱር አውሬ ከዚያው ይጠጣሉ።



እስኪ ጠይቁልኝ ከኒህ ከሁለቱ
ማነው የሚመረቅ እስከ ተፍጻሜቱ?
ለአንዲት ምሽት እራት ደግሶ ያበላው
ወይስ ንጹሕ ውሃ ቆፍሮ ያወጣው
ከሰው፣ ከከብት ተርፎ እንስሳን ያጠጣው
ቋሚ ንብረት ተክሎ ሰፈሩን ያረካው
አስቲ ጠይቁልኝ ለማን ነው ምረቃው?

ገ/ኢ. ጐርፉ።